# በኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ላይ የተዘረጋው
# የጥፋት መረብ እየተበጣጠሰ ነው!

ሰርጸ ደስታ

December 25, 2017 21:32

ያገሬ ልጆች ይህ ዛሬ የምናገረው ሲሆኑብን ስለቆዩና እየሆኑብን ያሉ ችግሮች እንደናስባቸው እኔ የራሴን እይታ ነው፡፡ በአለፉት 27 ዓመት የሄድንበት ሂደት አገርንና ሕዝብን ዛሬ ላይ አደጋ ላይ ጥሎ እያየን ነው፡፡ በእርግጥ ነው በእኔ ግንዛቤ ወና ሆኖ የተፈራው አደጋ አሁን እንደከሸፈ ይሰማኛል፡፡ ይሄውም ሕዝብ ለሕዝብ ይፋጃል አገር ትበተናለች ተብሎ የተፈራው ማለቴ ነው፡፡ ይሄ የሆነው በማናችንም ጥረት ሳይሆን እግዚአብሔር ይህ እንዳይሆን ስላረገ ነው፡፡ ብዙ ሕዝብ ለሕዝብ እንዲጫረስና አገርም እንድትፈርስ የተሰራባቸው ሴራዎች በተቃራኒው 27 ዓመት የተገነባውን የትንኮል ድር እየበጣጠሰው ነው፡፡ እነ ለማ መገርሳን በዚህ ወቅት በዚህ ሁኔታ ይመጣሉ ብሎ ማንም አላሰበም፡፡ ሕዝብም በተለይ የኦሮሞና አማራ ሕዝብ ለ 27 በመዋቅርና በፖሊሲ አንድነቱን ሲሸረሸር ቆይቶ አሁን በምናየው መልኩ እንዲህ ያለ ሕብረትን ይፈጥራል ብሎ የገመተ የለም፡፡ የጎንደሩ የአንድነት ደወል ዛሬ ከአገር አገር ተዳርሷል፡፡ ብዙ መከራዎች አልፈዋል፡፡ አሁም መከራዎች ይበልጥ እየጠነከሩ መጥተዋል፡፡ የሕዝብ ተስፋ ግን ከቀን ወደ ቀን እውን እየሆነና የዘመናት ምኞቱም እፈነጠቀ መጥቷል፡፡ ሊነጋ ሲል ይጨልማል እንደተባለው መከራው ይበልጥ ቢከፋም አሁን ሕዝብ አጸፋ ሊመልስ የሚችል አቅም እያጎለበተ ነው፡፡ የላመሪ ያለ አሌኝታ እንዲሁ ብቻውን ባዶ እጁን አደባባይ ፍትህ እያለ የወጣው ሕዝብ ዛሬ መሪዎችም፣ አቅም የሚሆኑ የታጠቁ ኃይሎችም ከጎኑ ቆመዋል፡፡ የመከራችን ዘመን አልፎ በአሳለፍናቸው 27 ዓመት እስካሁንም እያጣናቸው ያሉ ወገኖቻችንን የምናስበበት እኛም ዳግም መከራ እንዳይመጣብን መሠረታችንን የምናቆምበት ቀን እንደመጣ የሰማይ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ይረዳናል፡፡

አሁንም ግን የሚከተሉትን ጉዳዮች ሁላችንም ወደውስጣችን ተመልሰን እንደናስባቸው እወዳለሁ፡፡ ይህን ስል እኔ የተሰማኝን እንጂ ትክክል ነኝ የሚል ድምዳሜ አደለም፡፡ በእኔ አመክንዮ (ሎጂክ) ግን ትክክል ናቸው፡፡

የብሔር ማንነት ጉዳይ

ማንም ሰው ከተወለደበት ቤተሰብ ጀምሮ የእኔ የሚለው ዘር ሀረግ አለው፡፡ ቅርበቱም እንደዛው ከቤተሰቡ ጀምሮ ዘመዶቹ ጎሳዎቹ እያለ እየሳሳ ይመጣል፡፡ በሕዝብ ደረጃ ሲደርስ የዘር ማንነቱ ሳይሆን እንደሰው አብሮ ከሚኖራቸው ሁሉ ጋር በፍቅርና በሰላም መኖር ግድ ይለዋል፡፡ አልፎም በዘር ከተወለደው ይልቅ በሕወቱ ከአጋጠመው ወዳጁ ጋር ይበልጥ ትስስር ይኖረዋል፡፡ እየዘለቀም በጋብቻና በሌጆች አንደገና የበለጠ ዝምድናውን ወዳጅነቱን ያጠናክራል፡፡ እንዲህ በአለ መስተጋብር ሰዎች በአንድናትና በፍቅር በሰላም አብረው ይኖራሉ፡፡ የጋራ የሆኑ እሴቶች (ቫሊዩስ) ያፈራሉ፡፡ በእነዚህ እሴቶች ይተሳሰራሉ፡፡ በመዋቅርም ከመንድር ጀምረው እስከ አገር፣ አህጉር በመጨርሻም የዓለም ስብስቦች አንድ አካል ይሆናሉ፡፡ ይህ በሳይንስም እንዲህ ነው ተብሎ የማይተነተን ልዩ ሚስጢር ያለው የሰዎች የመኖር መስተጋብራዊ ስልት ነው፡፡ በዚህ መስተጋብር ገና ልጆች ሳለን ከቤተሰብ ውጭ ሌላ ሰው አናውቅም ቀጥሎ ከሰፈራችን ሰዎች ቀጥሎ አቅማችን ችሎ ከምንድርስባቸው ሌሎች ሕዝቦች እድሉ ሲገጥመንም በኣለም ዙሪያ እስከምንደርስባቸው ሕዝቦች ድረስ አብረን ለመኖር የጋራ እሴቶች እናኖራለን፡፡ ለእነዚህም ሕግ ሥርዓት እናወጣለን፡፡ አብሮ ለመኖር ቤተሰባዊ የሆነ የዘር ዝምድና ዋስትና አደለም፣ አንድ ሀይማኖት አንድ ቋንቋ መናገራችንም በፍጹም ከመነካከስ አያድነንም፡፡ አብሮ ለመኖር እግዚአብሔር አንድ ትዕዛዝ በሰው አእምሮ ውስጥ አኑሮዋል፡፡ ለራስህ ሊያደርጉብህ የማትፈልገውን በሌሎች አታድርግ፡፡ ይህን ተፈጥሮዋዊ ሕግ ግን ሕሊናችን እያዘዘን እንክደዋለን፡፡ ወዳጅ ስንሆን ደግሞ ሕጉ ለእኔ የሚያስፈልገኝ ለወዳጄም ያስፈልገዋልና እኔም እሱም ሊኖረን ይገባል ብለን የራሳችንንም ለወዳጃችን እናጋራለን፡፡ ይህ ከሁለት ጓደኛሞች ወይም ወንድማማቾች እስከ ተልቅ ማሕበረሰብ፣ አገራት ትስስር ድረስ የሚሄድ ነው፡፡

አንድ መንግስት አንደ መንግስት በሚመራው ግዛት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች እንዲቀራረቡና፡፡ በብዙ ነገር አንድነታቸው እንዲጠናከር ይጥራል፡፡ ያኔ አገዛዙ ይቀልለታል፡፡ ሕዝቡ በራሱ ጊዜ አብሮ ተባብሮ ስለሚኖር ለማስተዳደርም አይከብድምና፡፡ በአለፉት 26-7 ዓመት በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመው አሁንም ይበልጥ ተጠናክሮ የቀጠለው መንግስታዊ ስልጣን ባለው አካል እየተፈጸመ ያለው ሴራና ተግባር ግን በይፋ መርሀ ግብር ተቀርጾለት ሕዝብን ከሕዝብ በማባላት አገርን በማፈራረስና የአገርን ሀብት በመዝረፍ ላይ

የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ እጅግ ይገርማል፡፡ ይህ መዋቀራዊ ሴራ አድራጊዎች መፈጸማቸው ሳይሆን የእኛ ተቀብሎ ማስተናገድን ሳስብ ምን ሆነን ነው እላለሁ፡፡ አሁን ድረስ ይህ ያልገባን ብዙዎች ነን፡፡አማራነታችን ኦሮሞነታችን ትግሬነታችን ሌላም ማንነታችን ለዘመናት ሲኖሩ ብዙም ትዝ አላሉንም ነበር፡፡ ከብሔር ማንነታችን ይልቅ የሚበልጡብን የአካባቢ ማንነታችን ነበሩ፡፡ ኢጆሌ ባሌ፣ ኢጆሌ ጂማ፣ ኢጆሌ ሀረር፣ ኢጆሌ ነጆ፣ ተጉለቴ፣ ጎንደሬ ጎጃሜ ሆነን የብሔር ማንነታችንን ሳናስታውሰው ብዙ አመት በሰላም ኖረናል፡፡ ኢጆሌ ባሌ የባሌ ሰዎች ሁሉ በጋራ እንደመፈክር የሚናገሩት የማንነት ድምጻቸው ነበር፡፡ ሌላውም እንደዛው፡፡ ጎንደሬነትም ዘር አደለም፡፡ እኛን ብቻም አደለም ኢትዮጵያነትም ለእነዚህ ትልልቅ ብሔረሰባዊ ማንነት ከፋፍለው አንዱ ብሔር ወድሌላው ድንበር እንዳይሻገር የቆፈሩተን ገደል አጠሩብን፡፡ በዚህ ምክነያት መሠረታዊ ማንነቶቻችንንም (አካባቢ፣ ባሕል የመሳሰሉት) ብሔራዊ (ኢትዮጵያዊ) ማንነታችንም ወደሙና ሁሉንም በብሔር ማንነት ውስጥ ታሰርን፡፡

ዛሬ ሁላችንም አምነን የተቀበልንው የብሄር ማንነት እንግዲህ መሠረትም ጣሪያም የለሌው እንደሆነ አስተውሉ፡፡ እንደምሳሌ የኦሮሞ ብሔርን ለማብራሪያነት ልጠቀም፡፡ ለሁሉም ይሰራል ግን ስለምረዳውና ጥሩም ምሳሌ ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ከብዛቱም ከመልዓምድራዊ ሥፋቱም አንጻር በውስጡ ብዙ መሠረታዊ የማንነት ብዝሀነት አለው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ባህሎች፣ ሀይማኖቶችና ሌሎች ብዝሀነቱን የሚያሳዩ ማንነቶች አሉ፡፡ ትልልቅ የሚባሉት እንደ ኢሬቻ የመሳሰሉት ባሕላዊ ሥርዓቶች እንኳን ኦሮሞን በሙሉ የሚያሳትፉ አደሉም፡፡ በ27 ዓመት በምናየው ኦሮሞነት ዘመን ግን እየሆነ ያለው ኦሮሞ የተባለ ሁሉ እንደነዚህ ያሉ ሥርዓቶችን ማክበር አለበት አይነት አካሄድ ነው፡፡ አካሄዱም ዘመቻዊ አይነት ነው፡፡ ይህ አይነት አካሄድ ሥህተት ነበር፡፡ ብዝሀነትን ማጥፋትና ሁሉንም ወድ ኦሮሞነት መቀየር፡፡ በተመሳሳይ የዜግነት ማንነትም በዚሁ ለምሳሌነት በአነሳሁት የኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ብዥታ ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ አሁን በቅርብ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን እያጎላ ቢመጣም እስካሁንም ከብዥታው ያልተመለሰ ብዙ ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ ከሌሎች ጋር በመስተጋብር ሊያኖረው የሚችል ኢትዮጵያዊ ማንነቱን አጥቶ፣ ከሥር መሠረታዊ ብዝሀነቱን የሚጠብቅ ማንነቱን እጥቶ አየር ላይ በተንጠለጠለ ኦሮሞነት እንደተንሳፈፈ አስተውሉ፡፡ ይህ አይነቱ እውነት በሁሉም ብሔረሰቦች አለ፡፡ ልብ በሉ በአማራውም እንደዛው እንደሆነ፡፡ ጎነደርና ምንጃር የተራራቀ ባህል ነው ያላቸው፡፡ በየሕዝቡ ውስጥም የሀይማኖት ብዝሀነት አለ፡፡ እንግዲህ ከሥር ብዝሐነቶችን ያወደመ ከላይ ከሌሎች ጋር በመስተጋብር ዜግነታዊ ማነነትን ያጠፋ ውጤቱ ምን ይሁን፡፡ የኢትዮጵያዊ ማንነትን በክልል የብሔረሰብ ማንነት ስለተተካ አንድ ብሄር በፈለገው የኢትዮጵያ ክፍል ይኑር የሚለው አይሰራም፡፡ እንደይሰራም ሕገ ምንግስታዊ ሕግ ሆኖ እንዲወጣ እንደተደረገ አስተውሉ፡፡ የየክልሎቹን ሕገመንግስታት አንቀጽ 8 ና 9 አንብቡት በኋላ እመጣበታለሁ፡፡ ላለፉት በርካታ አመታት አንዱ ብሄር በሌላው የመኖር መብት እንደሌለው በተግባር እያየን (በደኖ፣ ጉራፈርዳ) ብዙም ትኩረት አልሰጠንውም፡፡ አሁን ላይ በሰፊው እያስተናገድንው እንገኛለን (የኦሮሞ-ሶማሌ ፍጅት)፡፡ አገር አታስፈልግም ሁሉም አሁን በታጠረለት የብሔር ማንነት ክልል ይኑር እንጂ ከተከለለት ውጭ እልፍ እንዳይል ቢባልና እስከመገንጠል እንደተባለው ብንገነጣጠል ከውስጥ በብሔር ማንነት አፍነን ያመቅናቸው የውስጥ ብዝሀነት ፈንድተው የብሔር ማንነታችንንም ብትንትኑን እንደሚያወጡት እናስተውል፡፡ በእኔ እምነት የብሔር ማንነትን ብቻ መሠረት ያደረገው የአስተዳደር መዋቅር (ፌደራሊዝም) መቼም ቢሆን አደገኛ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

የሕገመንግስታቱ ሰነዶች

የዋናው ማዕከላዊው ሕገመንግስት በውስጡ ብዙ አወዛጋቢ ብቻም ሳይሆን በግልጽ አገርንና ሕዝብን ለማፈራረስ የሚያንሳሱ አንቀጽ ማካተቱ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ክልሎችን አንዱ በሌላው ክልል መብት እንዳይኖረው የሚያደርግ ሕገ መንግስት እንዲኖራቸው አድርጎ ይሄው የማእከላዊው መንግስት ማንም ኢትዮጵያዊ በፈለገበት የኢትዮጵያ ክፍል መኖር መብት አለው ይላል፡፡ በተግባር ግን የተደረገው መብት የሚሆነው በሌላው ክልል ሄዶ መኖር ይቻላል ግን የደህነነት ዋስትናው ኃላፊነቱን መውሰድ ያለበት ራሱ መርጦ ሌላ ክልል የገባው ነው የሚል አንድምታ ነው፡፡

የየክልሎቹን አንቀጸ 8 ወይም 9 ስናነብ ግን ግልጽ ነው፡፡ አንዱ ብሔር በሌላው ብሄር ክልል የመኖር መብቱ የሚወሰነው በእንግድነት በሚሄድበት ብሄር በጎ ፍቃድ ነው፡፡፡ ምክነያቱም ክልሎች ለየብሔረሰቡ በግልጽ ተከፋፍለዋል፡፡ የክልሎቹ ሕገመንግስቶች የክልሉ ብሔር ብቻ አንጂ ሌላ በክልሉ የሚኖር ሕዝብን አያስተናግዱም፡፡ ክልሎች በግልጽ የኦሮሞ፣ የአፋር፣ የሶማሌ ሆነው ነው የተከለሉት፡፡ ለምሳሌ የኦሮሚያ ክልል በኦሮሚያ የሚኖሩ ሕዝቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሳይሆን የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ አንደሆነ ነው ሕገ መነግስት በተባለው ትልቅ ሰነድ በግልጽ የተጻፈው፡፡ እንብቡት፡፡ ሌሎችም እንደዛው፡፡ በአጋጣሚ ይሆን አስተውለውት ባይገባኝም የአማራ ክልል በክሉሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ይላል፡፡ እንግዲህ እንዲህ ባለ መሠረታዊ ሕጋዊነትን የተላበሰ ኢፍትሀዊነት እያለ ወደፊት በአንዱ ክልል በሌላው ብሔረሰብ ላይ ወንጀል የፈጸሙትን እንኳን እናቅርብ ቢባል ይህ ሕገመንግስታዊ ወንጀልን የመፈጸም መብት ሊተረጎምና ወንጀለኞች ሕጋዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትንና የሕዝቦችን አንድነት በይፋ እንዲጠናከር ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ያሉት በተለይ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት ሊመለከቱት የሚገባው አንዱ የክልሉ ሕገመንግስት ተብሎ የተቀመጠው ሰነድ ሊሆን እንደሚገባ አምናለሁ፡፡

የአገዛዙ የፖለቲካ ድርጅቶች

ከስያሜያቸው ብንነሳ ክልሎችን የወከሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ከላይ የጠቀስኩትን ሕገመንግስታዊ ግድፈትን በተግባር ለማዋል እንጂ የየክልሎቹን ሕዝቦች በአጠቃለይ እንደመንግስት ለማስተዳደር አይመስልም፡፡ በአዴን (ብሔረ አማራ ዴሞክራሳዊ ንቅናቄ) የክልሉ ሕገመንግስት በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ቢልም ይህ ድርጅት ከወከል አማራን እንጂ ክልሉን አይወክልም፡፡ ኦሕዴድ (የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሳዊ ድርጅት) ኦሮሞን እንጂ ሌላውን የክልሉ ሕዝብ አይወክልም፣ ሌላውም እንደዛው፡፡ ደህዴግ ምን አልባት የብሔርን ሳይሆን የክልሉን ስያሜ ስለያዘ ውክልናው የክልሉን ሕዝቦች ሁሉ ይሆናል፡፡ ሕወሀት(የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ) ከእንጭርሱ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል በተሰየመበት ሥያሜው ነው ያለው፡፡ እንግዲህ ወደፊት ፌደራሊዝምን ስናስብ ራሱ አንድን ብሔረስብ የወከለ ድርጅት በምን መስፈርት በክልሉም ሆነ በማእከላዊው መዋቀር እንደሚወክል አጠያያቂ ነው፡፡ በየትኛው ወረዳ እንኳን ቢኖን ወጥ የሆነ አንድ ሕዝብ የለምና፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ሥያሜ ራሳቸውን ከብሄር ማንነት አላቀው በአካባቢያዊ ወይም ከፍ ካሉ በክልሎን በሚወክል ሥያሜ ከዛም ዘለግ ከኣሉ አገሪቱን በሚወክል ሥያሜ መሠየም ከፍትሕ አንጻር ግድ ይላቸዋል፡፡ አንድን አካባቢ አወክላለሁ የሚል ፖለቲካ ድርጅት በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሁሉን አንጂ የእሱን ብሔር ብቻ ከሆነ ፍትሀዊነቱ ጥያቄ ውስጥ ነው፡፡ በአጠቃላይ ወጥነት አለ ቢባል እንኳን እንዲህ ያሉ አንድ ብሔር ወካይነት አስተሳሰቦች ወደፊትም ችግር ፈጣሪ ይሆናሉ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አንድነትና ሕብረት ማጠናከር ለብዙ ዘመን ከፍተኛ ስጋት የነበረው እርስ በእርስ የመፋጀትና አገር የመበተን አደጋ አሁን ላይ በጥሩ በሚባል ሁኔታ መልኩን ቀይሮ የሕዝቦችን አንድነትና አገራዊ ሉኣላዊነት መጠናከር ልዩ ተስፋ ሆኗል፡፡ ሆኖም አሁንም መታሰብ አለበት፡፡የሚከተሉትን እጠቁማሁ፡፡

የክልል መንግስታት አወቃቀራቸውንም ይሁን አስተዳደራዊ ፍልስፍናቸው ከብሔር ማንነት ጋር የተያያዘ ሳይሆን የክልሉን ሕዝብ ሁሉ አንደመንግስት ህዝቤ በሚል ፍልስፍናና መዋቀራዊ መሠረት ያለው ማደረግ ቋንቋንና ሌሎች ማሕበረሰባዊ እሴቶች በመንግስት ደረጃ ተጨባጭ የሆነ መበልጸግ እንዲኖራቸውና እንደአመቺነታቸው ለአስተዳደራዊ ግብኣት ከመጠቀም ውጭ ብሔረሰባዊ ይዘት እንዳይኖራው ማድረግ፡፡ ብዙዎች ቋንቋ መቻላቸው የሌላ ብሔር በመሆናቸው ብቻ ከብዙ የሚኖሩበት ክልል ሙብት የተገለሉ ናቸውና፡፡
ጸረ-ሕዝብና ጸረ-ፍትሕ የሆኑ “ሕጋዊ” ሰነዶችን በይፋ ነቅሶ ማውጣት በእነዚህ ሰነዶች ዝግጅት የተሳተፉ አካላትን ለፍርድ ማቅረብ፡፡

ለምሳሌ የጸረ-ሽብር ሕግ

በጸረ-ሕዝብና ጸረ-ፍትህ ” ሕጎች” እየተጠቀሱ የተከሰሱና በእስር የሚገኙ ወገኖች በአስቸኳይ እንዲለቀቁና አስፈላጊው ካሳ ሁሉ እንዲከፈላቸው ማድረግ፡፡

የብሔራዊ ደህንነት መዋቅሩን ሙሉ በሙሉ አፍርሶ በአዲስ መተካት፡፡

በፌደራል ፖሊስ፣ ማገሚያ ቤቶች፣ በመከላከያ የመዋቅር ሰንሰለቶች፣ አንዲሁም በአንዳንድ የሲቪል ተቋማት ለምሳሌ የዜግነትና ኢሚግሬሽን አየር መንገድ የመሳሰሉ መ/ቤቶች አላግባብ በብሔር ማንነታቸው እንዲሰሩ የተደረጉ ሁሉ ቦታውን በሚመጥኑና ያለምንም አድልዖ ተወዳዳሪ በሚሆኑ አንዲተኩ፡፡ ከዚህ በፊት በአድልኦ ገብተው ሲሰሩ የቆዩ የመወዳደር ሙብት ኤኖራቸውም፡፡ ምክነያት ያለአግባብ በመመደባቸው ሕጋዊ አይሆኑም፡፡

ፓርላማው አሁን እንደጀመረው ወደፊትም የሚሾማቸውን ባለስልጣናት ጠ/ሚኒስቴሩን ሳይቀር የማውረድና አገርን በአግበብ ለማስተዳደር በሚወሰኑ ጉዳዮች ወሳኝ አንዲሆን፡፡
አመሰግናለሁ!
ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይጠብቅ! አሜን!

ሰርጸ ደስታ